# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል

## 14 ኛ ሳምንት

## ሙሴ

**ዓላማ**

❖ ስለ ሙሴ ሕይወት እና መልካምነት መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**

❖ ***«ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» ዮሐ.15፥13***

**ምንባባት**

❖ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቁ እና ዘዳግም፣

**መግቢያ**

❖ ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ወደ ነፃይቱ ምድር ያወጣ ነው፡፡ ሲወለድም ከእሰራኤል የተወለደ ወንድ ሁሉ እንዲሞት አዋጅ በተነገረበት ወቅት ነበር፡፡ እናቱ ግን እንደተወለደ ለሦስት ወራት ከደበቀችው በኂላ በሳጥን አድርጋ በወንዝ ዳር አስቀመጠችው የፈርኦን ልጅ አግኝታው ወሰደችው እንደልጅ አድርጋም አሳደገችው፡፡ እናቱ እንደሞግዚት ሆና ታሳድገውና ታስተምረው ስነበረም ዕብራዊ መሆኑን አወቀ፡፡ ሕዝቡ በባርነት እንዴት እንደሚሠቃዩ እያየም አደገ፡፡ አንድ ቀንም አንድ ዕብራዊ እና ግብፃዊ ሲጣሉ አይቶ ግብፃዊውን ገደለው፡፡ ይህ ዜና በግብፅ ተሠማ፤ ስለዚህም ሙሴ ከፈርኦን ቤት ሸሽቶ ምድያም በተባለች ምድር መኖር ጀመረ፡፡ በዚያም አግብቶ ሁለት ልጆች ወለደ፡፡ የአማቹ የዮቶርን ከብቶች ሲያግድ ነበር በኮሬብ (የእግዚአብሔር ተራራ) በሚባለው በቁጥቋጦው መሐል በሚነድ እሳት እግዚአብሔር የተገለጠለት ከዚህ ቀጥሎ ሙሴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ሕይወት እንማራለን፡፡ ይህም እግዚአብሔር ከተገለጠለት በኂላ ነው፡፡

**ትምህርቱ**

❖ **ሙሴ መልካም ልብ ያለው ሰው ነበር፡፡** ስለሕዝቡ መከራ ያለውን ሀብትና ሥልጣን ሁሉ ትቶአል፡፡ ሕዝቡ እየተሠቃየ በንጉሡ ቤተመንግሥት መኖር አላስደሠተውም፡፡ በዚህም እስራኤልን ነፃ ሊያወጣ እግዚአብሔር ሾመው፡፡

❖ **ሙሴ ትጉህ ሰው ነበር፡፡** እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ ሊያወጣ ወደፈርኦን እንደሚልከው ሲነገረው፡፡ ሙሴ ***«ወደ ፈርኦን የምሄድ የእሰራኤልንም ልጆች ነፃ የማወጣ እኔ ማን ነኝ»*** ዘጸ.3÷11 ነበር ያለው፡፡ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር እንደሆነና የሚናገረውን ቃል እንደሚሰጠው እና ሕዝቡንም በእርሱ በእግዚአብሔር ኃይል እንደሚያወጣ ነገረው፡፡

❖ **ሙሴም ወደ ፈርኦን ሄዶ እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሀል አለው፡፡** እግዚአብሔር እንዳዘዘው በትሩን ወደ ምድር ጥሎ እባብ ሲሆን እንደ መጀመሪያ መልክት ለፈርኦን አሳየው፡፡ ፈረኦንም አዲስ ነገር እንዳለሆነ በመግለፅ ጠንቋዮች አምጥቶ ተመሳሳይ ነገር አደረገ፡፡ የሙሴ በትር ግን ሌሎቹን ዋጠቻቸው፡፡ ፈርኦን ግን ሕዝቡን አልቀቀም በዚህም እግዚአብሔር አሥር መቅሠፍቶችን አመጣባቸው፡፡ በመጨረሻም ፈረኦን ሕዝቡ እንዲሄዱ ፈቀደ፡፡

❖ **ሙሴ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲያስቡ በተደጋጋሚ ያሳስባቸው ነበር፡፡** እነርሱ ግን ሁሌም ይጠራጠሩና እግዚአብሔርን ያስቆጡ ነበር፡፡ ወደ ቀይ ባህር ሲወጡም የፈርኦን ጦር ተከትሎዋቸው ነበር ሕዝቡ በሙሴ ላይ አለቀሱ፡፡ ልትገድለን አወጣኸን አሉት ሙሴ ግን ***«የእግዚአብሔር ማዳን እዩ»*** አላቸው ባህሩንም በበትሩ መታው፤ ለሁለት ተክፍሎላቸውም ተሻገሩ በጉዞአቸውም ታላላቅ ተዓምራትን ያደርግላቸው ነበር፡፡ መና ከሰማይ፣ ውሃ ከአለት፣ በጦርነት ድሎችን እየሠጠም ወደ ተስፋይቱ ምድር አደረሳቸው፡፡

❖ **ሙሴ የጾምና ፀሎት ሰው ነበር**፡፡ ሙሴ 10ቱን ትዕዛዛት የተፃፈባቸውን የድንጋይ ፅላቶች ሲቀበል 40 ቀን 40 ሌሊት ጾሞ ነበር፡፡

❖ **ሙሴ ከራሱ ደህንነት ይልቅ ስለሕዝቡ ያስብ ነበር**፡፡ እንዴ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ስለአመፀ እግዚአብሔር ይህን ሕዝብ አጥፌቼ በሌላ ሕዝብ ላይ እሾምኃለሁ አለው፡፡ ሙሴ ግን በሌላ ሕዝብ ላይ መሾም እንደማይፈልግና ሕዝቡን እንዲያድን ተማጸነ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ከሕይወት መጽሐፍ ደም ስሠኝ ነበር ያለው፡፡ እግዚአብሔር የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ ሕዝቡን አዳነ፡፡

❖ **ሙሴ በቅዱሳን አማላጅነት ያምን ነበር፡፡** ሙሴ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲያድን ሲማጸን እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማለላቸውን መሃላ አስቦ እንደያድናቸው ነበር የደለየው፡፡ እግዚአብሔርም ተቀብሎ ፈጸመለት፡፡

❖ **እግዚአብሔር ቅዱሳንን እንድናከብር ይፈልጋል፡፡** ሕዝቡ በሙሴ ላይ ሲያጉረመርም እግዚአብሔር ተቆጥቷል፡፡ የማራቸውም በሙሴ ምልጃ ነበር፡፡ ወንድሙን አሮንን የገሠጸው እኅቱ ማርያምንም በለምፅ የመታት ወዳጁና ቅዱሱን ሙሴን ስለተቃወሙበት ነበር፡፡

❖ **ሙሴ ወደቃልኪዳኒቱ ምድር ከመግባቱ በፊት በ 120 ዓመቱ ሞተ፡፡** እግዚአብሔር ምድሪቱን በረከቱን አሳየው፣ እስራኤልም ለአንድ ወር አለቀሱለት፡፡ ሙሴም እያሱ ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲያስገባ ከመሞቱ በፊት ተክቶላቸው ነበር፡፡

❖ **ሙሴ አምስቱን መፅሐፍት ፅፏል**፡፡ እነርሱም ስነፍጥረትን፣ ሕግን እንዲሁም ከግብፅ የመውጣታቸውን ታሪክ ይዘዋል፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የሙሴ እናት በሣጥን አድርጋ ወንዝ ዳር ያስቀመጠችው ለምን ነበር? የት አደገ?
2. ሙሴ የዕብራውያንን እምነትና ባሕል እንዴት ተማረ?
3. ሙሴ እሰራኤል በቀይ ባህር ሲያለቅሱበት ምን አላቸው?
4. ሙሴ አሥርቱን ትዕዛዛት ከመቀበሉ በፊት ስንት ቀንና ሌሊት ጾመ?
5. እግዚአብሔር ለሙሴ መጀመሪያ ሲገለጥለት እንዴት ነበር? ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነፃ ታወጣለህ ብሎ ሲልከው የሙሴ መልስ ምን ነበር?
6. እስራኤል በማመፃቸው ሊያጠፋቸው ከወሰነ በኂላ እግዚአብሔር የራራላቸው ለምን ነበር?

**ይቆየን፡፡**